# የ COVID-19 ክትባት አስተማማኝነት፡- ማወቅ ያለብን ነገር

Vaccinate WA

CovidVaccineWA.org

## ክትባቶቹ ለደኅንነት አስተማማኝ ናቸው

በአሜሪካ ውስጥ ያሉን የ COVID-19 ክትባቶች በአሜሪካ ታሪክ[1] የደኅንነት ክትትል ተደርጎባቸው ያለፉ ናቸው። ሁሉም ክትባቶች በ U.S. Food and Drug Administration (FDA፣ የምግብ እና መድሀኒት አስተዳደር)ሙሉ በሙሉ ጸድቀዋል ወይም ፍቃድ አግኝተዋል—ማለትም FDA ምንም የደህንነት ስጋቶች አላገኘም። ገለልተኛ የሆኑ ከፍተኛ ባለሙያዎች (ኤክስፐርቶች) የተደረጉትን ጥናቶች በተጨማሪ ገምግመዋቸው ምንም ዓይነት አሳሳቢ ሁኔታዎችን አላገኙባቸውም።

ሕዝቡ እየተጠቀመባቸውም እያለ ክትባቶቹ አሁንም ለደኅንነት አስተማማኝ እና ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቀጣይ ክትትል እየተደረገባቸው ነው። ደኅንነትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለማጣራት አሜሪካ በሥራ ላይ ያሉ በርካታ መከታተያ ዘዴዎች አሏት እና አስጊ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ወዲያውኑ ለማወቅ ትችላለች።

## ክትባቶቹ ውጤታማ ናቸው

አንዳንዱ ክትባት ከሌላኛው ይልቅ የተሻለ እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ መረጃን ዐይተው ሊሆን ይችላል። በሰዎች ላይ የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉም አሁን ማግኘት የሚቻሉት ክትባቶች COVID-19ን ለመከላከል በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ እንደሆኑ ያሳያሉ። በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች ስለ ተሞከሩ በክትባቶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ለማወዳደር አስቸጋሪ ናቸው። አንዳንዶቹ ሌላው ሳይቀር በ COVID-19 የተለያዩ የሕመም ደረጃዎች ላይ የተሞከሩ ናቸው።

ሙሉ ክትባት ከወሰዱ በኋላ አሁንም በ COVID-19 ሊያዙ ይችላሉ ሆኖም ግን በጣም ለመታመም ወይም ወደ ሆስፒታል የሚያስገባ የሕመም ደረጃ ለመድረስ ያልዎት ዕድል አናሳ ነው። በሰዎች ላይ ከተደረጉ ሙከራዎች ውስጥ እያንዳንዳቸው ክትባቶች ቢያንስ በ 85 በመቶ ያክል **ከባድ** የሆነ የ COVID-19 በሽታን በመከላከል ረገድ ውጤታማ ነበሩ። ክትባቶቹም ብዙ ሰዎች **ማንኛውንም** የ COVID-19 በሽታ ምልክቶች እንዳያሳዩ አድርገዋቸዋል።

- Johnson & Johnson (Janssen)፣ 74 በመቶ
- Pfizer-BioNTech፣ 95 በመቶ
- Moderna፣ 94 በመቶ

## የጎንዮሽ ጉዳቶች የተለመዱ ናቸው

ክትባቱ በ COVID-19 እንዲያዙ አያደርጎትም። ሆኖም ግን እንደ ሌሎች ክትባቶች ሁሉ አንዳንድ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊሰሙዎት ይችላሉ። እነዚህ ክትባቱ በትክክል እየሠራ ለመሆኑ የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። በሁለት ጊዜ ለሚሰጡ ክትባቶች፣ በሁለተኛ ጊዜ በሚሰጠው ክትባት ወቅት የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ከበድ ሊሉ ይችሉ ይሆናል። የሚቻል ከሆነ፣ በቂ ዕረፍት ለራስዎት ይስጡ እና ከተከተቡ በኋላ ባለው አንድ ወይም ሁለት ቀን እስከሚያገግሙ ድረስ ዕረፍት ያድርጉ። ሁለት ጊዜ መከተብ ለሚያስፈልጋቸው የ COVID-19 ክትባቶች፣ ሁለተኛውን ክትባት መከተብዎን ያረጋግጡ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሁለተኛውን ክትባትዎን ካልተከተቡ በቀር ሙሉ በሙሉ ከበሽታው ራስዎትን መጠበቅ አይችሉም።

### ክትባቱን በተከተቡበት ክንድዎ ላይ፡-

- ሕመም ስሜት
- መቅላት
- ማበጥ



### በመላ ሰውነትዎ ላይ፡-

- የድካም ስሜት
- የራስ ምታት
- የጡንቻ ሕመም
- ብርድ፣ ብርድ ማለት
- ትኩሳት
- ማቅለሽለሽ



[1] Centers for Disease Control and Prevention, "Safety of COVID-19 Vaccines (የ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝነት)"። ማርች 25፣ 2021፣ መሥመር ላይ (ኦንላይን) እዚህ ላይ ይገኛል፡- https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/vaccines/safety/safety-of-vaccines.html (በእንግሊዘኛ ብቻ የሚገኝ)።

## የአለርጂ ምልክቶች

በክትባቱ ምክንያት የሚከሰቱ የአለርጂ ምልክቶች በጣም አልፎ፣ አልፎ የሚከሰቱ ናቸው፣ ሆኖም ግን ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ምናልባት የአለርጂ ምልክት ቢያጋጥምዎት ለማየት ክሊኒኩ እርስዎ ከተከተቡ በኋላ ለ15 ደቂቃ ያሉበትን ሁኔታ የሚያይ ይሆናል። የሕክምና ባለሙያዎቹ ችግር ቢያጋጥም ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እና እንዴት እርስዎን ማገዝ እንደሚችሉ ለማወቅ በሚያስችላቸው ደረጃ የሠለጠኑ ናቸው።

ከክሊኒኩ ወጥተው ከሄዱ በኋላ የአለርጂክ ስሜት ከተሰማዎት ወደ 911 ይደውሉ። የአለርጂክ ስሜቶች ምልክቶች እነዚህን ያካትታሉ:- ለመተንፈስ መቸገር፣ የፊትዎ እና የጉሮሮዎ ማበጥ፣ ፈጣን የልብ ምት፣ በመላው ሰውነት ላይ መጥፎ ሽፍታ መታየት፣ እንቅልፍ፣ እንቅልፍ ማለት እና የድካም ስሜት።

## ለደኅንነት የሚያሰጉ ሁኔታዎችን መከታተል እንድንችል ያግዙን

ማናቸውንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት ሪፖርት ለማድረግ ወደ V-safe በዚህ አድራሻ ይመዝገቡ:- vsafe.cdc.gov (በእንግሊዘኛ ብቻ የሚገኝ)። የእርስዎ ተሳትፎ ክትባቶቹን ለሁሉም ሰው ለደኅንነቱ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ እንድንችል ያግዘናል።

እርስዎ ወይም የእርስዎ ክትባት አገልግሎት አቅራቢ ከባድ የሆኑ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ወደ Vaccine Adverse Event Reporting System (VAERS፣ ጎጂ የክትባት ሁኔታ ዘገባ ስርዓት) ሪፖርት ማድረግ ትችላላችሁ። አዝማሚያዎችን ወይም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለመከታተል FDA፣ Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት) እና Washington State Department of Health (DOH፣ የዋሺንግተን ግዛት የጤና መምሪያ) VAERS ን ይጠቀማሉ።

በ vaers.hhs.gov (በእንግሊዘኛ ብቻ የሚገኝ) ላይ ጥቆማዎን ማስገባት ይችላሉ።

## ከተለያዩ ዘሮች እና ጎሣዎች የተውጣጡ ሰዎች ሙከራዎቹ ላይ ተሳትፈዋል

ሳይንቲስቶች እያንዳንዱን ክትባት በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ሞክረዋቸዋል።







[2]Food and Drug Administration. "FDA Briefing Document: Pfizer-BioNTech COVID-19 Vaccine", Vaccines and Related Biological Products Advisory Committee (ክትባቶች እና ተጓዳኝ የስነ ሕይወት ምርቶች አማካሪ ኮሚቴ) ስብሰባ። ዲሴምበር 10፣ 2020፣ መሥመር ላይ (ኦንላይን) እዚህ ላይ ይገኛል:- https://www.fda.gov/media/144245/download (በእንግሊዘኛ ብቻ ይገኛል)።
[3]Food and Drug Administration. "FDA Briefing Document: Janssen Ad26.COV2.S Vaccine for the Prevention of COVID-19", Vaccines and Related Biological Products Advisory Committee ስብሰባ። ፌብሩዋሪ 26፣ 2021፣ መሥመር ላይ (ኦንላይን) እዚህ ላይ ይገኛል:- https://www.fda.gov/media/146217/download (በእንግሊዘኛ ብቻ ይገኛል)።
[4]Food and Drug Administration. "FDA Briefing Document: Moderna COVID-19 Vaccine", Vaccines and Related Biological Products Advisory Committee ስብሰባ። ዲሴምበር 17፣ 2020፣ መሥመር ላይ (ኦንላይን) እዚህ ላይ ይገኛል:- https://www.fda.gov/media/144434/download (በእንግሊዘኛ ብቻ ይገኛል)።

ክትባቱ ለሕፃናት፣ ለነፍሰጡር ሴቶች እና ሌላ የጎንዮሽ በሽታዎች ላሉባቸው ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ ነው። ብዙ ሰዎች እየተከተቡ ሲመጡ፣ በደኅንነት ጉዳይ እና በጎንዮሽ ጉዳቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ እናገኛለን። መረጃዎች የ COVID-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ያሳያሉ፣ እና ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እምብዛም አይደሉም።

## ክትባት ለመከተብ የሚያሳስብዎት ነገር ካለ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪን ወይም የክሊኒክ ሠራተኛን ያነጋግሩ።



### አለርጂዎች

- Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከላት) በክትባት ውስጥ ያለ ንጥረ ነገር አለርጂ ለማይሆንበት ለማንኛውም ሰው ይመከራል።
- በ COVID-19 ክትባቶች ምክንያት የሚያጋጥሙ የአለርጂ ችግሮች ብዙውን ጊዜ polyethylene glycol (PEG) እና polysorbate በሚባሉ በክትባቱ ውስጥ የሚገኙ ስቦች አማካይነት እንደሚፈጠሩ ተደርጎ ይታሰባል።
- ክትባቶቹ ልክ በምግብ ላይ እንዳሉት አለርጂን የሚፈጥሩ ተመሳሳይ ንጥረ ነገሮች የሏቸውም በመሆኑም የ COVID-19 ክትባት በሚወስዱበት ጊዜ ሌሎች የአለርጂ ምክንያቶች ስጋት መሆን የለባቸውም። ለምሳሌ፣ ክትባቶቹ ከእንቁላል፣ ከወተት ተዋፅኦ፣ እና ምግብ እንዳይበላሽ ከሚያደርግ ኬሚካል ነጻ ናቸው።

### ሥነ ምግባር

የ COVID-19 ክትባት ንጥረ ነገሮች ለደኅንነት አስተማማኝ ናቸው እንዲሁም ክትባቶቹ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊ ናቸው። የ Johnson & Johnson ክትባት አንዱ ክትባት ከ35 ዓመታት በፊት ከተመረጡ ውርጃዎች ከተገኙ ሕዋሳት በላብራቶሪ ውስጥ እንዲጎለብቱ ከተደረጉ ንጥረ ነገሮች የተሠራ ነው። ኩፍኝ፣ ሩቤላ እና ሄፐታይተስ ኤን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ክትባቶች በተመሳሳይ መንገድ የተዘጋጁ ናቸው። ከእነዚህ ክትባቶች መካከል ማናቸውም ህያው የሰው ልጅ ሕዋሳት (የፅንስ ሕዋሳትን ጨምሮ)፣ የ COVID-19 ቫይረስ፣ የወተት ተዋፅኦ፣ ምግብ እንዳይበላሽ የሚያደርግ ኬሚካል፣ ወይም የዓሣማ ተዋፅኦ እና ጌላቲንን ጨምሮ ምንም ዓይነት የእንስሳት ተረፈ ምርቶች በውስጣቸው የለባቸውም። ክትባቶቹ በእንቁላል ውስጥ እንዲጎለብቱ አልተደረጉም እንዲሁም ምንም ዓይነት እንቁላል በውስጣቸው የለባቸውም።

### የጤና ችግሮች

- የ COVID-19 ክትባቶች የጤና ችግሮች ባሉባቸው ሰዎችም ላይ ለደኅንነት አስተማማኝ እና ውጤታማ እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ። በእያንዳንዱ የክትባት ሙከራዎች ላይ ከተሳተፉ ሰዎች መካከል ከሃያ እስከ 45 በመቶ የሚደርሱት እንደ ከልክ በላይ የሆነ ውፍረት፣ ስኳር በሽታ፣ የልብ በሽታ፣ የጉበት በሽታ እና ኤችአይቪ ያለባቸው ሰዎች ነበሩ።
- ደካማ በሽታን በተፈጥሮ የመከላከል አቅም ወይም የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ችግር ባለባቸው ሰዎች ላይ ክትባቱ ስላለው ውጤት በተመለከተ ውስን የሆነ የደኅንነት ማረጋገጫ መረጃ (ውሂብ) አለን። CDC እነዚህ ሰዎች በ COVID-19 ከተያዙ ከፍተኛ የሆነ በበሽታው የመጎዳት ዕድል ስላላቸው ክትባቱን እንዲወስዱ አጥብቆ ይመክራል።
- የእርግዝና እና የወሊድ ህክምና ባለሙያዎች ለእርጉዞች፣ ለሚያጠቡ ወይም ለማርገዝ ላሰቡ ሰዎች የ COVID-19 ክትባትን እንዲወስዱ ይመክራሉ። መረጃዎች የ COVID-19 ክትባቶች በእርግዝና ጊዜ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ያሳያሉ። በእርግጥ አንዳንድ ጥናቶች ክትባት የወሰደች ወላጅ በእርግዝና እና ጡት በማጥባት የ COVID-19 ፀረ እንግዳ አካላትን እንኳን ወደ ልጇ ልታስተላልፍ እንደምትችል ያሳያሉ። ነፍሰ ጡር ሰዎች ሞትን ጨምሮ በ COVID-19 ለሚከሰት ከባድ በሽታ ተጋላጭ ናቸው። ክትባቶቹ ከሁሉ የተሻለ መከላከያ ናቸው።

Washington State Department of Health

**DOH 348-799 February 2022 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት እንዲቀርብልዎት ለመጠየቅ፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደዚህ ይላኩ፡-civil.rights@doh.wa.gov።